# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

**የኢትዮጵያ ለም መሬት በማንለብኛነት ለሱዳን መስጠቱን ኢዴኃኅ ያወግዛል**

ሕወሓት/ኢሕአዴግና የሱዳን መንግሥት ባለፈው ዓመት ባደረጉት የድብቅ ስምምነት ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪ.ሜ. ርዝመትና ከ20 እስከ 50 ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ለም የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረትም የሱዳን ሀብታም ገበሬዎች የኢትዮጵያን ለም መሬቶች በሰፊው ማረስ ጀምረዋል፡፡ የሱዳን ወታደሮች በተሰጣቸው መሬት ላይ ካምፕ አቋቁመው ወታደሮች አስፍረዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ቤታቸው እየተቃጠለ ንብረታቸው እየወደመ ከእርሻ ቦታቸው ተፈናቅለው ተባረዋል፡፡ ኢትዮጵያውን በሱዳን ወታደሮች ታስረው ወደ ሱዳን መወሰዳቸውንም ለማወቅ ችለናል፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የአቶ መለሰ መንግሥት በማን አለብኛነት ለሱዳን መንግሥት የኢትዮጵያን መሬት መስጠቱን በጽኑ ያወግዛል፡፡

በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ወሰን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሁለቱን አገሮች ሲያከራክር እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከሁለቱ አገሮች ተውጣቶ የተቋቋመው የጋራ ኮሚሽን በድንበሩ ጉዳይ ለረዥም ዓመታት ሲመክርና ሲከራከር የቆየ እንደነበር ባይዘነጋም በድንበር መካለል በኩል የተደረሰ ስምምነት እንዳልነበረም ይታወቃል፡፡ በንጉሡ ዘመነ መንግሥትም ሆነ በደርግ ጊዜ አንድ ክንድ መሬት እንኳን ለሱዳን የተሰጠበት ሁኔታ እንዳልነበር ግልጽ ነው፡፡ የአቶ መለሰ መንግሥት ከሱዳን መንግሥት ጋር ያለውን ወዳጅነት ለማጥበቅና የሱዳን መንግሥት የተሟላ ትብብር በሥልጣን ላይ ለመቆየት እንዲያስችለው በማያወላውል መንገድ የኢትዮጵያ የሆነውን ወደ 1600 ኪ.ሜ. ርዝመት ያለውና ከ 20 -50 ኪ.ሜትር ስፋት ያለውን ሰፊ ለም የእርሻ መሬት ለሱዳን አስረክቧል፡ ይህ ስምምነት ቀደም ብሎ በምስጢር የተደረገ ቢሆንም የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች የኢሕአዴግ መንግሥት የተባለውን መሬት ለሱዳን ለማስረከብ መስማማቱን በይፋ ገልጸዋል፡፡

ከኢሕአዴግ መንግሥት መሬት የተቸረው የሱዳን መንግሥትም የኢትዮጵያን ለም መሬቶች እየሸነሸነ ለሱዳን ሀብታም ገበሬዎች አድሎ እያሳረሰ ከመሆኑ ባሻገር ወታደሮችን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አስገብቶና ካምፕ መስርቶ ኢትዮጵያውያንን ከቀያቸው እያፈናቀለና እያባረረ ቤትና ንብረታቸውን እያቃጣለ ይገኛል፡፡ ፡፡ በአብዱራፊ ፥ በቋራ ነፍስ ገበያና በሌሎች ቦታዎች በርካታ የኢትዮጵያን የእርሻ ቤቶች ተቃጥለዋል፥ ንብረቶች ተዘርፈዋል፡፡ የሀገራችንን መሬት አናስነካም ከቤት ንብረታችን አንወጣም ያሉትንም ወገኖቻችን አስሮ ወደ ሱዳን በመወሰድ እያሰቃያቸው ይገኛል፡፡ ባለፉት ጥቂት ቀናት ብቻ ከ30 የማያንሱ ወገኖቻችን ከእርሻ ቦታቸውና ከቀያቸው በሱዳን ወታደሮች እየተያዙ ወደ ሱዳን ምድር ከተወሰዱ በኋላ፣ በእስር ቤት በመሰቃየት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ቁጥር ከ60 በላይ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት የሚሰጡም በርካታ ናቸው፡፡ በየቦታው ያለው ሕዝባችን በባዕድ ወታደሮች የሚደርስበትን ጥቃት ለመቋቋም ሲንቀሳቀስ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ወታደሮች የወገኖቻችን ድኅንነት ከመጠበቅና ከወገን ጎን ቆሞ ጥቃቱን ከመከላከል ፈንታ

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ከጎረቤት መንግሥት ጋር ግጭት ማድረግ እንደማያስፈልግ ጥብቅ ትእዛዝ እየሰጡ መሆናቸውና ከሱዳን ወታደሮች ጋር ግጭት ለማድረግ በሚንቀሳቀሱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ወደ ኋላ እንዳይሉ በማስፈራሪያ መልክ እየገለጹ መሆናቸው ተረጋግጧል። የባዕድ ኃይል በሀገራችን ምድር ሲሰፍር እሰይ አበጀህ የሚል የመንግሥት አካልና የወገኑ ንብረት ሲዘረፍ፥ ወገኑ ቀዬውና ከመሬት ላይ በባዕድ ወታደሮች ሲባረርና ወገኑም በባዕድ ኃይል ተይዞ ወደ ባዕድ አገር ሲወሰድ ከባዕድ ጋር የሚተባበር መንግሥት ኢትዮጵያዊነቱና ለኢትዮጵያ መቆሙ አጠራጣሪ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም።

ለአገር የሚቆረቆር፥ አገር ወዳድ የሆነና ለሕዝብ የተመረጠና ለሕዝብ ተጠሪ የሆነ መንግሥት የአገርን ለም መሬት ለባዕድ አገር ለመስጠት ከሕዝብ ጀርባ አይዋዋልም፥ የተደበቀ ስምምነት አያደረግም። በወሰን ጉዳይ ለውጥ የሚያስፈልግ ቢሆን እንኳ በግልጽ ለሕዝብ ተነገሮ ሕዝብ ተስማምቶበት፥ በሕዝብ ይሁንታና በሕዝብ ውሳኔ ይሆናል እንጂ ማንም የመንግሥት ሥልጣን ይዤለሁ የሚል ኃይል የኢትዮጵያን ግዛት አሳልፎ ለመስጠት ሥልጣንም ሆነ መብት የለውም። አድርጎ ከተገኘም በወንጀለኛነትና በኃላፊነት ከመጠየቅ የሚያመልጥ አይሆንም። በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ላይ ወጥቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብት አፍኖ አሸባሪ አምባገነን አገዛዙንን በሕዝብ ላይ ጭኖ ሕዝባችንን እየበዘበዘና እያሳቃየ የሚገኘው ሕወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ምድር ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ ለሌላ አሳልፎ ሲያስረክብ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። የዛሬ 17 ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃዱና አስተያየቱ ሳይጠየቅ ኤርትራ ነፃ መውጣት አለባት የሚል ደብዳቤ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም በሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪ በአቶ መለሰ ዜናዊ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መጻፉን የምናስታውሰው ነው። የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን ከኤርትራ ነፃ አውጭ ድርጅቶች ጋር ወታደራዊ ትብብር ፈጥሮ የደርግን መንግሥት መጣሉና ከዚያም ኤርትራ እንድትገነጠል ከፍተኛ የዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሲያደርግ የቆየው ሥልጣን ለመያዝም ሆነ ሥልጣኑን ለማረጋጋት የሻዕቢያ ትብብርና ርዳታ ያስፈልገው ስለነበረ መሆኑ ግልጽ ነው። በሥልጣን ላይ መቆየትና ጥቅም ከማጋበስ በስተቀር ስለሀገርና ወገን ቅንጣት ታህል የማይገደው ይኸው አሸባሪው አምባገነን ቡድን አሁን ለሱዳን ባዕድ መንግሥት የሀገሩን ለም መሬት ያስረከበበት ምክንያቶች ወደፊት ግልጽ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖርም ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የተቃዋሚ ኃይሎች እንቅስቃሴ በሱዳን ውስጥ መሠረት እንዳይኖረው የሱዳን መንግሥት እንዲተባበረው ለማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው።

ለሀገራችን ውስብስብ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘትም ሆነ ዳር ድንበሯ የተጠበቀ፥ ሉዓላዊነቷ የተራገገጠ ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በሥልጣን ላይ ያለውን አሸባሪ አምባገነን አገዛዝ ሥልጣን ከሕዝብ በሚመነጭበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በትግል መተካት አማራጭ የሌለው ቢሆንም መሠረታዊው ሕዝባዊ ትግል እየቀጠለ በአሁኑ ወቅት በሱዳን የተወሰደውን የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ለማስመለስ በያለበት ትግሉ መፋፋም አለበት። በሕገ ወጥ መንገድ ሥልጣን የያዘው ሕወሓት ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማይወክል በመሆኑ ከሱዳን ጋር ያደረገውም ስምምነት ሕገ ወጥ ነው፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት የለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩ በባዕድ ስተደፈር በርካታ መስዋእትነት በመክፈል ዳር ድንበሩን አስክብሯል፥ የተወሰደበትንም መሬት አስመልሷል። በሱዳንና በኢትዮጵያ ወሰን አካባቢ የነበረውን መሬት አስመልክቶ ሕዝባችን ከእንግሊዝ፥ ከደርቡሽም ከሱዳኖችም ጋር ተናንቆ ዳር ድንበሩን አስከብሮ መቆየቱ ታሪክ የሚያረጋግጠው ነው ። በአሁኑ ወቅት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የአገራችን ዳር ድንበር ለመጠበቅም ሆነ በማን አለብኝነት የተወሰደብንን መሬት ለማስመለስ ሁለ ገብ ትግል ማድረግና መንቀሳቀስ ይኖርብናል። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ያለው ሕዝባችን ጉዳዮን ተረድቶ በሰላማዊ ስልፍም ሆነ ሌሎች አመች በሆኑ መንገዶች ተቃውሞውን እንዲያሰማ ማቀናጀትና ማስተባበር፥ የውጭ መንግሥታት ድጋፍን ለማግኘት የተቃዋሚ ኃይሎችና የሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የተቀነባበረ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ የሚያድርጉበትን ሁኔታ መፍጠር፥ ከእርሻ ቦታቸው የተፈናቀሉት ኢትዮጵያን የሞራልም ሆነ የማቴሪያል እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ መሻት፥ በሱዳን መንግሥት በማንአለብኛነት

ታፍነው ተወስደው በሱዳን እስር ቤት የሚገኙ ወገኖቻችን ባስቸኳይ ተፈትተው ወደ አገራቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ ለመፍጠር መታገል የወቅቱ ግንባር ቀደም ተግባሮቻችን መሆን አለባቸው። የተባበረረና የተቀናባበር ትግል ካካሄድን የተወሰደብን መሬት ባጭር ጊዜ ውስጥ አስመልሰን ከአባቶቻችን የወረስነው ዳር ድንበር ለማስከበር የምንችል መሆኑ ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

በተባበረ ትግል የተወሰደብን መሬት ይመለሳል!

በትግላችን ዳር ድንበራችን ይከበራል፥ የአገራችን ሉዓላዊነትም ይከበራል!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት

ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም.